የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የካሳ ክፍያ አከፋፈል ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታኅሣስ 2006

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የኮርፖሬሽኑ አመሰራረት 2
የኮርፖሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር፤- 2
የካሳ አገማመትና አከፋፈል ሥልጣንና የሥራ ድርሻ 3
ንብረት መገመትን በተመለከተ፤- 3
የንብረት ገማች ኮሚቴን በተመለከተ፣ 3
በአዋጅ ቁጥር 455/97 የኮርፖሬሽኑ ኃላፊነት፤ 4
አዋጅ ቁጥር 455/1997 የማስፈጸም ስልጣንን በተመለከተ፣ 4
የኮርፖሬሽኑ አደረጃጀትና የሰው ኃይል 4
የሰው ኃይል 5
የፋይናንስ ምንጭ 5
የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ 5
የኦዲቱ አካባቢ 5
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (audit issue) 6
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፣ 6
የኮርፖሬሽኑ፣ የከተማ፣ የወረዳ እና የገማች ኮሚቴ የካሳ ክፍያ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (process description) 8
ክፍል ሁለት 9
ግኝቶች 9
ሀ. እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ለሚከፈል ካሳ የአከፋፈል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥን በተመለከተ፤ 9
አዋጅ ቁጥር 455/1997 መሰረት በማድረግ አገር አቀፍ የካሳ አከፋፈል ቀመር እና የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ 9
የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር እና መመሪያ በየጊዜው ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ፣ 10
ለ. የካሳ ክፍያን ለማስፈጸም፣ለመቆጣጠር፣ለመከታተልና ለመገምገም ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የሆነ መሆኑን በተመለከተ፣ 11
የካሳ ክፍያ ንብረት ለመገመት ተገቢው ሙያ ያለው ኮሚቴ የተቋቋመና የገማች ኮሚቴ አባላት ስለካሳ ግመታ ገለጻ ወይም ስልጠና ያገኙ መሆኑን በተመለከተ፣ 11
የካሳ ክፍያ ግምት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን በተመለከተ፣ 12

ለልማት እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኙ ንብረቶችን የሚመለከት መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣ 13
መሬት ለልማት ሥራ እንዲለቀቅ ሲወሰን መሬቱ የሚለቀቅበት ጊዜ እና የካሳው ግምት ለባለይዞታው በቅድሚያ መገለጹንና መሬቱ በወቅቱ መለቀቁን በተመለከተ፣ 13
ንብረትን የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪን የሚሸፍን ካሳ መከፈሉን በተመለከተ፣ 15
ለልማት ሥራ የሚፈለገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ለአላቸው አካላት መድረሱን በተመለከተ፣ 16
ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለሚለቀቅ መሬትና ንብረት የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎች ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል (በኮርፖሬሽኑ) የሚሸፈን መሆኑን በተመለከተ፡- 17
የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣ 17
ክፍል ሦስት 19
መደምደሚያ 19
ክፍል አራት 21
የማሻሻያ ሃሳቦች 21
አባሪ 1፡- የኦዲት መገምገሚያ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) 24
አባሪ 2፡የኮርፖሬሽኑ፣ የከተማ፣ የወረዳ እና የገማች ኮሚቴ የካሳ ክፍያ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (process description) 26
አባሪ 3፡ በሄክታር የሚመረቱ ምርቶች ልዩነት የሚያሳዩ ሰንጠረዦች 27
1. የኮሚቴውን እና የስታትስቲክስ ጽ/ቤት በሄክታር የሚመረቱ ምርቶች ልዩነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ 27
2. የኮርፖሬሽኑን እና የኮሚቴውን በሄክታር የሚመረቱ ምርቶች ልዩነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ 27
3. የኮርፖሬሽኑ ጥናት እና የኮሚቴው የካሳ ክፍያ ግምት የዋጋ ልዩነት 28

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የአገሪቱ ከተሞችም ሆነ በገጠር የሚከናወኑ የመሰረተ ልማት፣ የኢንቨስትመንት፣ የመኖሪያ ቤት ግንባታ እና ሌሎች የልማት ሥራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መጥተዋል፡፡ ለእነዚህ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚውል የመሬት አቅርቦት አስፈላጊ ስለሆነ የበፊት ባለይዞታዎችን ተገቢውን ካሣ በመክፈል ከይዞታቸው እንዲነሱ ይደረጋል፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ ንብረትን በሚመለከት በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የሚረዳ አዋጅ ቁጥር 455/1997 ወጥቷል፡፡ አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዳ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በቁጥር 135/1999 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
2. አዋጁ በሁሉም ክልሎች መከበሩን፣ መከታተልና ማረጋገጥ እንዲሁም ክልሎች አዋጁና ደንቡን ለማስፈጸም እንዲችሉ የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነትን በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 12 ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥቷል፡፡ ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችን አፈጻጸም የሚረዳ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ለክልሎች የተሰጠ ሲሆን፤ የሚፈለገው መሬት እንዲለቀቅ ለባለይዞታዎች ካሳ የመክፈል ወይም እንዲከፈል የማድረግና አቅም በፈቀደ መጠን የመልሶ መቋቋም ድጋፍ የማድረግ፣ እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኘውን ንብረት በሚመለከት መረጃ የመያዝ ኃላፊነት ደግሞ የወረዳዎችና የከተማ መስተዳደሮች ኃላፊነት ነው፡፡
3. በዚህ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት እና የመሠረተ ልማት ተግባር ላይ በዋነኛነት ከሚሳተፉ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን አንዱ ሲሆን፣ ኮርፖሬሽኑ በአዋጅ የተሰጡትን ዓላማዎች ለማሳካትና ቀጣይነት ባለው መልኩ ህዝቦችን እና ባለሀብቶችን በሚፈልጉት ደረጃ የኃይል ተጠቃሚ ለማድረግና ከአገራችን ዕድገት ጋር ተያይዞ የመጣውን የኃይል ፍላጎት ለማርካት በዘርፉ በየጊዜው ሰፊ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
4. በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለውን የኃይል ፍላጎት ለማርካት ኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ኃይል የማመንጨት አቅም ያላቸውን የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ግንባታ፤ የኃይል ማስተላለፊያ መሥመሮች ዝርጋታ እና የማከፋፈያ ጣቢያዎች (Substations) ግንባታ በስፋት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር የኃይል አቅርቦቱ ከኃይል ፍላጎቱ ቀድሞ እስኪገኝ ድረስም እነዚሁ የግንባታ ሥራዎች ተጠናክረው በዘርፉ ያለውን ልምድ በማጎልበት የኅብረተሰቡን የኢኮኖሚ ዕድገት፤ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤን ባገናዘበ

መልኩ አስተማማኝና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈልና የመሸጥ አገልግሎት በመስጠት በአገሪቱ ለሚገኝ ለሁሉም ነዋሪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራትና ብቃት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት መስጠትና ተወዳዳሪ የኤሌክትሪክ ኤክስፖርተር መሆን የሚቀጥሉ የኮርፖሬሽኑ ግቦች ናቸው፡፡

5. ኮርፖሬሽኑ እነዚህ ግቦችን ለማሳካት እና የአገሪቱን የኃይል ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ ከፍተኛ ግንባታዎች እና የመስመር ዝርጋታዎችን ለማከናወን የሚፈልገውን ቦታ ለማስለቀቅ ከየሥፍራው ለሚነሱ ነዋሪዎች ንብረቶችና ሰብሎች ማካካሻ የሚሆን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ እየመደበ የካሳ ክፍያ በየጊዜው ይፈፅማል፡፡

የኮርፖሬሽኑ አመሰራረት

6. በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት የተጀመረው በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን መንግስት በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ሲሆን የመጀመሪያው ጀነሬተር በ1890 ለቤተመንግሥት አገልግሎት መስጠት ጀመረ፣ በመቀጠልም የመጀመሪያው የውሃ ኃይል ማመንጫ በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ- መንግሥት በ1904 ዓ/ም አቃቂ ወንዝ ላይ ተግንብቶ አገልግሎት ለመስጠት በቃ፡፡

7. በአገራችን የኤሌክትሪክ ኃይልን በማመንጨት፣ በማስተላለፍ፣ በማከፋፈልና ለተጠቃሚ ደንበኞች የኤሌክትሪክ መብራትና ኃይልን በመሸጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ አገልግሎቱን በማስፋት የሀገሪቱን ህዝቦች ተጠቃሚ ለማድረግ በ1949 ዓ/ም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክና መብራት ኃይል ባለሥልጣን በሚል ስያሜ ተቋቋመ፡፡ በመቀጠልም በደንብ ቁጥር 18/1989 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በሚል ስያሜ እንዲቋቋምና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት እንዲተዳደርና በቦርድ እንዲመራ ተደርጓል፡፡በደንብ ቁጥር 170/2002 የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ዋና ተቆጣጣሪ እንዲሆን ተሰይሟል፡፡

የኮርፖሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር፣-

8. ኮርፖሬሽኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 170/2002 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቶታል፡-

   ✓ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ማስተላለፍ፣ ማከፋፈል እና መሸጥ ሥራዎችን ያከናውናል፣

- ✓ የተለያየ ዓይነትና ደረጃ ያላቸውን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ማስተላለፊያ፣ ማከፋፈያ እና የኤሌክትሪክ ኃይል መቆጣጠሪያ ግንባታ ሥራዎችን ጨምሮ የአዋጪነት ጥናት፣ የማማከር፣ እነዚህን ተግባራት በራሱ አቅም ለማከናወን ባልቻለም ጊዜ ከአገር ውስጥ እና ውጪ አማካሪዎች ቀጠሮ ያሰራል፤
- ✓ በተያያዘው የኤሌክትሪክ ሲስተም ውስጥ ያለውን ብሔራዊ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ያስተዳድራል፤
- ✓ መንግሥት በሚያስቀምጠው ውሣኔና አቅጣጫ መሠረት ከኃይል አመንጪዎች ጋር የኃይል ድርድርንና ግዥ ይፈጽማል፤
- ✓ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ከየሀገራቱ መንግሥታት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት ለድንበር ተሻጋሪ የኃይል ማስተላለፍ ሥራ ያከራያል፡፡ ሲያስፈልገውም በተመሣሣይ ሁኔታ ከሌሎች ሀገራት ይከራያል፤
- ✓ ከጎረቤት ሀገሮች፣ከአህጉራዊ እና አለም አቀፋዊ የኃይል መስመሩን በማገናኘት በመንግሥታት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት በሚወሰን ዋጋ የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ውጪ ሀገር ይልካል፤ ሲያስፈልገው ይገዛል፣
- ✓ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት እንዲኖር ለማድረግ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ፤ ቦንድ ይሸጣል፤ በዋስትና ያሲዛል፤ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል ይደራደራል ይፈራረማል
- ✓ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ይሠራል፡፡

የካሳ አገማመትና አከፋፈል ሥልጣንና የሥራ ድርሻ

9. በአዋጅ ቁ.455/97መሰረት

ንብረት መገመትን በተመለከተ፤-

እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬት ላይ የሚገኝ ንብረት ካሳ የሚወጣውን አገር አቀፍ ቀመር መሰረት በማድረግ በተመሰከረላቸው የግል ወይም የመንግሥት ተቋማት ወይም ግለሰብ፣ አማካሪዎች የሚገመት መሆኑ፣

የንብረት ገማች ኮሚቴን በተመለከተ፣

10. የሚለቀቀው መሬት የሚገኘው በገጠር ሲሆን ንብረቱ የሚገመተው የወረዳው አስተዳደር በሚያቋቁመውና ተገቢው ሙያ ባላቸው ከአምስት ያልበለጡ አባላት ባሉት ኮሚቴ መሆኑ፣

11. የሚለቀቀው መሬት የሚገኘው በከተማ ውስጥ ሲሆን ንብረቱ የሚገመተው የከተማው አስተዳደር በሚያቋቁመውና ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት በሚገኙበት ኮሚቴ መሆኑ፣ ተገልጿል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 455/97 የኮርፖሬሽኑ ኃላፊነት፤

12. የኮርፖሬሽኑ ኃላፊነት ለሥራው የሚፈለገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ሥፍራ የሚያሳይ መረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት አዘጋጅቶ መሬት ለማስለቀቅ ሥልጣን ላላቸው አካላት የመላክና የማስፈቀድ፣ የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለተደረጉ ባለይዞታዎች በአዋጅ ቁ/455/97 መሰረት በገማች ኮሚቴ ተተምኖ የቀረበለትን የካሳ መጠን መክፍል ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 455/1997 የማስፈጸም ስልጣንን በተመለከተ፣

13. የአዋጅ ቁጥር 455/97 ድንጋጌዎች በሁሉም ክልሎች መከበራቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ፣ ለክልሎች አዋጁን ለማስፈጸም እንዲችሉ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የማድረግ፣ እንዲሁም በአዋጁ መሰረት ለሚወሰን ካሳ አገር አቀፍ የአተማመን ቀመር አግባብ ካላቸው ሌሎች የፌዴራል መንግሥት አከላት ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ እንዲጸድቅ የማድረግ፣ ስልጣን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መሆኑ በአዋጁ ላይ ተገልጿል፡፡

<u>መመሪያ የማውጣት ስልጣንን በተመለከተ፣</u>

14. አዋጅ ቁጥር 455/97 እና በአዋጁ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ለክልሎች ተሰጥቷል፡፡

የኮርፖሬሽኑ አደረጃጀትና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

15. በኦዲቱ የኮርፖሬሽኑን አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና በስሩም አስራ አንድ የተለያዩ የሥራ ሂደት ቡድኖች (ኮርፖሬት ማኔጅመንት፣ የኃይል ማመንጫ ግንባታ፣ የኃይል ማመንጫ፣ የከፍተኛ መስመር ግንባታ፣ የትራስሚሽን ኦፐሬሽን፣ የዲስትሪቢዩሽን ሲስተም፣ የሽያጭ፣ አገር አቀፍ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም፣ ኮርፖሬት የሰው ኃይል፣ የኮርፖሬት ፋይናንስና ሰፐላይ ቼን እና ኮርፖሬት አገልግሎቶች የሥራ ሂደት ቡድኖች) ነበሩት፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ኮርፖሬሽኑ አደረጃጀቱን በመቀየር ላይ ይገኛል፡፡

የሰው ኃይል

16. ኮርፖሬሽኑ በኅዳር 2006 ዓ.ም.10,586 ወንድ እና 2,158 ሴት በድምሩ 12714 ቋሚ ሠራተኞች፣ 4,164 ወንድ እና 441 ሴት በድምሩ 4,605 የኮንትራት ሠራተኞች በአጠቃላይ 17,319 ሠራተኞች ነበሩት፡

የፋይናንስ ምንጭ

17. ኮርፖሬሽኑ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከመንግሥት በየዓመቱ ከሚመደብ በጀት፣ እራሱ ከሚሰበስበው ገቢ፣ ከቦንድ ሽያጭ፣ እንደዚሁም ከእርዳታና ብድር የሚያገኝ ሲሆን ያለፉት ሦስት በጀት ዓመታት ለመደበኛና ለካፒታል ወጪ የተመደበለት በጀት እና በስራ ላይ የዋለው ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ዓ.ም	የተመደበ በጀት		ጠቅላላ የተመደበ በጀት	ጥቅም ላይ የዋለ		ጥቅም ላይ የዋለ ጠቅላላ ወጪ	
	መደበኛ	ካፒታል		መደበኛ	ካፒታል	በብር	በፐርሰንት
2003	2,379,663,000	36,069,530,000	38,449,193,000	1,950,074,000	16,397,033,000	18,347,107,000	47%
2004	1,923,000,000	36,605,000,000	38,528,000,000	1,659,756,000	28,907,805,000	30,567,561,000	79%
2005	2,080,000,000	42,847,750,000	44,927,951,000	1,840,535,000	29,524,123,000	31,364,658,000	70%

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

18. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኮርፖሬሽኑ የሚከናወነው የካሳ ክፍያ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋ ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

የኦዲቱ አካባቢ

19. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ለማስተላለፍ፣ለማከፋፈል እና ለመሸጥ አገልግሎት የሚለቀቅ የመሬት ይዞታና ንብረት የካሳ አከፋፈል፣ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣

የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (audit issue)

20. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና አራት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነሱም፡-

1. እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ለሚከፈል ካሳ የአከፋፈል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤

2. የካሳ ክፍያን ለማስፈጸም፣ለመቆጣጠር፣ለመከታተልና ለመገምገም ኃላፊነት የተሠጣቸው አካላት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የሆነ መሆኑን መገምገም፣

   2.1. የንብረት ገማች ኮሚቴ ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት የሚገኙበት መሆኑን ማረጋገጥ፤

   2.2 የወረዳና የከተማ አስተዳደሮች የካሳ ክፍያን በማስፈጸም ረገድ ኃላፊነታቸውን ቀልጣፋና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ማረጋገጥ

   2.3 ካሳ ከፋዩ መ/ቤት የተሰጡትን ኃላፊነቶች ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ማከናወኑን ማረጋገጥ፤

   2.4 የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሥራውን ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ማከናወኑን ማረጋገጥ፤

የሚሉት ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፣

21. ከላይ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) እና አራት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመገምገም የሚያስችል 23 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡)

<u>**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ**</u>

22. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን

መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003-2005 ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት እና የ2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

23. የዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና በናሙና በተመረጡ ኮርፖሬሽኑ የካሳ ክፍያ በፈጸመባቸው የጣና በለስ- ባህር ዳር፣ የባህርዳር-ደብረማርቆስ-አዲስ አበባ፣ የወላይታ ሶዶ- አዲስ አበባ 400 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላለፊ መስመር ዝርጋታ ፕሮጀክቶች፣ የአሉቶ ላንጋኖ ጂኦተርማል ፕሮጀክት፣ የአላማጣ-መሆኒ- መቀሌ እና የቆቃ-ሁርሶ-ድሬዳዋ የ230 ኪ.ቮ የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክቶችን፣ መረጃዎች በመከለስ፣ ለኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎችም መጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡

24. በተጨማሪም በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉ መስተዳደር ጽ/ቤት፣ የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣንን፣ የባህርዳር ከተማ መስተዳደር፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያ እና የይልማና ዴንሳ ወረዳዎች መስተዳድሮችንና የገማች ኮሚቴ አባላትን፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የክልሉ መስተዳደር ጽ/ቤት፣ በግብርና ቢሮ የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣንን፣ በጉራጌ ዞን የምስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ መስተዳደሮችንና የካሳ ገማች ኮሚቴ አባላትን ካሳ ክፍያን በሚመለከት መረጃቸውን በመከለስና ቃለመጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡

25. በፌዴራል ደረጃ የካሳ ክፍያን በበላይነት እንዲያስተባብር በአዋጅ ቁጥር 455/1997 ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ኃላፊዎች ካሳ ክፍያን አስመልክቶ ምንም እንዳልሰሩ በቃል ከመግለጽ ውጭ ለኦዲቱ መረጃ ለመስጠትም ሆነ ቃለ መጠይቅ ለመመለስ በተደጋጋሚ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

የኮርፖሬሽኑ፣ የከተማ፣ የወረዳ እና የገማች ኮሚቴ የካሳ ክፍያ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (process description)

ኮርፖሬሽኑ የአዋጭነት፣ የአካባቢና የማህበራዊ ሁኔታ ግምገማ ፣ እና የመልሶ ማቋቋሚያ መርሀ ግብር ጥናቶች ያዘጋጃል

ለሚሰራው ፕሮጀክት አንድ የሥራ አስፈጻሚ በቦታው ይመድባል፣ ሥራውን ለመጀመር የሥራውን አካባቢና መጠኑንም የሚያሳዩ ባለሙያዎች ይመደባሉ፡፡

ስለሚነሱ ቤቶች፣ ሰብሎች እና ሌሎች ንብረቶች ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚገልጽ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የክልል፣ የከተማና የወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤቶች ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡

ከተነሺው ማህበረሰብ ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት ይደረጋል፡፡

በሚመለከተው የወረዳ ወይንም የከተማ መስተዳድር የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

የተቋቋመው የካሳ ገማች ኮሚቴ የካሳ ክፍያ ግምት በማውጣት ዝርዝሩን ለኮርፖሬሽኑ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

ባለንብረቱ የሚነሳበትን ጊዜ የተተመነውን የካሳ ክፍያ መጠን የሚገልጽ እና በዚህ መሰረትም የወረዳው፣ የከተማ መስተዳድሩ ትብብር እንደሚያደርጉ የሚገልጽ መተማማኛ ተዘጋጅቶ ባንብረቱ እንዲፈርም ይደረጋል፡፡ የተፈረመው ማስረጃም በሚመለከተው የከተማ ወይንም የወረዳ አስተዳደር ማህተም እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

ባለመብቱ አስፈለጊውን ማስረጃ በሟሟላት በካሳ ገማች ኮሚቴ የተተመነለትን ገንዘብ በኮሚቴው ፊት በመቅረብ ከኮርፖሬሽኑ ፈርሞ እንዲወስድ ይደረጋል፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

ሀ. እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ለሚከፈል ካሳ የአከፋፈል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥን በተመለከተ፤

አዋጅ ቁጥር 455/1997 መሰረት በማድረግ አገር አቀፍ የካሳ አከፋፈል ቀመር እና የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

26. አዋጅ ቁጥር 455/1997ን መሰረት በማድረግ ለልማት ሥራ ለሚፈለግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት ለሚከፈል የካሳ ግምት አገር አቀፍ ቀመር ሊወጣ ይገባል፡፡ ክልሎችም አዋጁንና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችን መሰረት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት አለባቸው፡፡ በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የካሳ ግምት ለሚሰሩ ገማች ኮሚቴዎች ሊደርስና በእርሱ መሰረት የካሳ ግምት ሊሰራ ይገባል፡፡
27. አዋጅ ቁጥር 455/1997ን ለማስፈጸም ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ስለሚከፈል ካሳ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/1999ን አውጥቷል፡፡ በናሙና ከታዩት ሁለት ክልሎች ውስጥ አዋጁንና ደንቡን መሰረት በማድረግ የአማራ ክልል ብሔራዊ መንግስት የአፈጻጸም መመሪያ በመጋቢት 2003 ያወጣ ሲሆን፣ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ግን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የአፈፃፀም መመሪያ እንዳላወጣ ለማወቅ ተችሏል፡፡
28. በኦዲቱ ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ክልላዊ መንግስት በሀድያ ዞን ሌሞ ወረዳ ለወላይታ ሶዶ- አዲስ አበባ 400 ኪ.ቮ. የኃይል መስመር ዝርጋታ ለሚነሱት ንብረቶች የተቋቋመው የካሳ ገማች ኮሚቴ የወጣውን አገር አቀፍ ተመን መሰረት ሳያደርግ አስልቶ ብር 7,240,101 (ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሺህ አንድ መቶ አንድ ብር) የካሳ ክፍያ ገምቶ ክፍያ እንዲፈፀም ጥያቄ አቅርቦ እንደነበረ፣ ሆኖም ኮርፖሬሽኑ በአገር አቀፍ ቀመሩ መሰረት ክፍያው በጣም የተጋነነ በመሆኑ ድጋሚ በቀመሩ መሰረት ሂሳቡ እንዲሰላ በተደረገ ማጣራት የተገመተው የካሳ ክፍያ ወደ ብር 3,387,967 (ሦስት ሚሊዮን ሥስት መቶ ሰማኒያ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሰባት ብር) ዝቅ ተደርጎ የተሰላና በዚሁ መሰረት ክፍያው የተፈፀመ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

29. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የአማራ ክልል ቢዘገይም የካሳ ክፍያ የአፈፃፀም መመሪያ በ2003 ዓ.ም ማውጣታቸውንና ለሚመለከታቸው አካላት በመመሪያው ላይ ሥልጠና መስጠታቸውን ሲገልጹ፣ የደቡብ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት የተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ደግሞ በ2004ዓ.ም ረቂቅ የአፈፃፀም መመሪያው የተዘጋጀ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልፀደቀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

30. የአዋጅ ቁጥር 455/97 ድንጋጌዎች በሁሉም ክልሎች መከበራቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ለክልሎች አዋጁን ለማስፈጸም እንዲችሉ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የማድረግ እንዲሁም በአዋጁ መሰረት ለሚወሰን ካሳ አገር አቀፍ የአተማመን ቀመር አግባብ ካላቸው ሌሎች የፌደራል መንግስት አካላት ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ እንዲፀድቅ የማድረግ ስልጣን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መሆኑ በአዋጅ ላይ ቢገለፅም እንደየተጨባጭ ሁኔታቸው ክልሎች የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያወጡ ለማድረግ የተከናወነ የድጋፍና የክትትል ሥራ መኖሩን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተጠይቆ በቃል ካሳ ክፍያን በተመለከተ የሰራው ምንም ሥራ እንደሌለ ከመግለጽ ውጭ በኦዲቱ ወቅት ማቅረብ ለፈለግነው መጠይቅ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

31. አገር አቀፍ የካሳ ክፍያ አተማመን ቀመርን መሰረት ያደረገ መመሪያ በሁሉም ክልሎች እንዲወጣ አለመደረጉና ይህንንም በተመለከተ በአዋጁ ድጋፍና ክትትል የማድረግ ስልጣን የተሰጠው የፌድራል አካል ክትትልና ድጋፍ ያለማድረጉ በካሳ አከፋፈል ሥርዓቱ ላይ እና በታሰበው የልማት ስራ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር እና መመሪያ በየጊዜው ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ፣

32. የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሊዘጋጅ እና የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የአማራ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መስተዳደሮች ካሳ ክፍያን አስመልክቶ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የሚጠቀሙበት ቀመር ያለፉትን አምስት አመታት አማካኝ ዋጋ በመውሰድ መሆኑና የዋጋው ልዩነቱም በጣም የተራራቀ የሚያደርገው በመሆኑ በካሳ ክፍያ ወቅት ከፍተኛ ችግር እንደገጠማቸው እና ቀመሩ እንደገና መታየት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

34. ስለጉዳዩ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ኃላፊዎች ካሳ ክፍያን አስመልክቶ በሚኒስቴር

መ/ቤቱ ስለተከናወኑ ሥራዎች በሰነድ እና በቃለ መጠይቅ መረጃ እንዲሰጡ በቁጥር ፌዋኦ123/274 በ24/07/05 በተጻፈ ደብዳቤ የተጠየቁ ቢሆንም በቃል ካሳ ክፍያን አስመልክቶ ምንም ስራ አለመስራታቸውን ከመግለጽ ውጭ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው መጠይቅ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

35. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ካሳ ክፍያን በተመለከተ በአዋጁ የተሰጠውን ኃላፊነት አለመወጣቱ ካሳ ክፍያን አስመልክቶ በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡት ህጎች በአግባቡ ተግባራዊ እንዳይሆኑ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ለ. የካሳ ክፍያን ለማስፈጸም፣ለመቆጣጠር፣ለመከታተልና ለመገምገም ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የሆነ መሆኑን በተመለከተ፣

የካሳ ክፍያ ንብረት ለመገመት ተገቢው ሙያ ያለው ኮሚቴ የተቋቋመና የገማች ኮሚቴ አባላት ስለካሳ ግመታ ገለጻ ወይም ስልጠና ያገኙ መሆኑን በተመለከተ፣

36. ለልማት ሥራ የሚፈለገው መሬት የሚገኝበት የወረዳው ወይንም የከተማው አስተዳደር ለሚከናወነው የካሳ ግምት ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት የሚገኙበት የካሳ ገማች ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ የሚቋቋሙት የካሳ ገማች ኮሚቴ አባላት ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት በአዋጅ ቁጥር 455/97 እና ደንብ ቁጥር 135/99 በሚመለከት ገለጻ ወይም ስልጠና እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

37. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የጣና በለስ-ባህርዳር፣ ባህርዳር-ደብረማርቆስ-አዲስ አበባ እና የወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ 400 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላላፊ መስመር ከሚያልፉባቸው በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያ እና የይልማና ዴንሳ ወረዳዎች እና የባህርዳር ከተማ መስተዳድር፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የጉራጌ ዞን ምስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ የተቋቋሙት ገማች ኮሚቴዎች ከተለያዩ ዘርፎች የተወጣጡ ባለሙያዎች ቢሆኑም ካሳ ግመታን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በተመለከተ ገለጻ ወይም ሥልጠና እንዳልተሰጣቸውና በራሳቸው መረዳት የካሳ ግመታውን ይሰሩ እንደነበረ የካሳ ገማች ኮሚቴዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአማራ ክልል የባህርዳር ከተማ መስተዳድር፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያ እና የይልማና ዴንሳ ወረዳ መስተዳደሮችና የገማች ኮሚቴ አባላት ስለአዋጁም ሆነ ደንቡ እውቀት ባይኖራቸውም

የምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን አቸፈር ወረዳ የጣና በለስ- ባህርዳር የኃይል መስመር ዝርጋታ ሲከናወን ለተነሱት አርሶ አደሮች በወረዳው የተሰራውን ግምት መነሻ አድረገው ግምቱን መስራታቸውን፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጉራጌ ዞን የምስቃን ወረዳ እና በሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ ገማች ኮሚቴ አባላት ደግሞ ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤትና ከከተማ መስተዳደሮች መረጃ እየጠየቁ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት እንደሞከሩ ገልጸዋል፡፡

39. ለካሳ ክፍያ ንብረት ለመገመት የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የገማች ኮሚቴው አባላት ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ስለአዋጁና ደንቡ ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ ባለመደረጉ የካሳ ክፍያው ግምት አዋጅንና ደንቡን ታሳቢ ያደረገ እንዳይሆን ክፍያው የየወረዳውን ምርትና ምርታማነት ያላገናዘበ በመሆኑ እና በየጊዜው ተነሺዎች ቅሬታ እንዲያቀርቡ በማድረጉ፣ የካሳ ግምት በሚከናወንበት ወቅት የሁሉንም ወገኖች መብትንም ሆነ ግዴታን ጠብቆ ተግባራዊ ለማድረግ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

የካሳ ክፍያ ግምት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን በተመለከተ፣

40. ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚነሱ ባለይዞታዎች የሚከፈለው የካሳ ግምት በበቂ መረጃ ላይ የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ የካሳ ክፍያ ግምት ከመሰራቱ በፊት የፕሮጀክቱ አዋጭነት ጥናትና የሚያርፍባቸው ቦታዎች መልሶ ማቋቋሚያ መርሀ ግብር (Resettelement action plan) ሲጠናም ሆነ የካሳ ገማች ኮሚቴው በልማት የሚነሱ ንብረቶችን የግምት ሥራውን ሲሰራ በበቂ መረጃ ላይ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡

41. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ተከለሱ ከካሳ ክፍያ ጋር የተያያዙ አላማጣ- መሆኒ- መቀሌ እና ቆቃ -ሁርሶ- ድሬዳዋ የ230 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ፕሮጀክቶችና፣ የአሉቶ- ላንጋኖ ፕሮጀክት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን ስታትስቲካዊ መረጃ የማይጠቀሙ ከመሆኑም በላይ የኮርፖሬሽኑ የአዋጭነት ጥናት እና የገማች ኮሚቴ የካሳ ግምትም አንድ አለመሆኑ ታይቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 3 ላይ ተያይዟል፡፡

42. ይህንንም በተመለከተ በናሙና የታዩ ክልሎች የየወረዳው ገማች ኮሚቴዎች ከወረዳና ከከተማ መስተዳደሮች መረጃ እየጠየቁ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ግን ልዩነቱ ለምን እንደተከሰተ ምላሽ አልሰጡም፡፡

43. ኮርፖሬሽኑ በአሰጠናው የአዋጭነት ጥናት ላይ ያለው መረጃ እና የካሣ ገማች ኮሚቴዎች የተጠቀሙባቸው መረጃዎች የተለያየ በመሆኑ የተፈጸመው የካሳ ክፍያ ኮርፖሬሽኑ ለካሳ ክፍያ ከያዘው በጀት ጋር ልዩነት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የካሳ ክፍያ

ግምቶች በበቂ ጥናት እና የምርታማነት መጠን ላይ በተመሰረተ በቂ መረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ለሌላ ልማት ሥራ ሊውል የሚችል ገንዘብን አላግባብ በካሳ ክፍያ ስም እንዲባክን ያደርጋል፡፡

ለልማት እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኙ ንብረቶችን የሚመለከት መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣

44. ለልማት አገልግሎት እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬትና በመሬቱ ላይ የሚገኙ ንብረቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአዋጅ እና በደንቡ መሰረት የከተማው ወይንም የወረዳው አስተዳደር ሊይዝ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህርዳር ከተማ መስተዳደር፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያና የይልማና ዴንሳ ወረዳዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በጉራጌ ዞን የምስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ ለኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ማስተላለፊያ ሥራ ለማከናወን የተነሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ የተጠናቀሩ መረጃዎች በከተማው ወይንም በወረዳው አስተዳደር ያልተያዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

46. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ካሳ የተከፈላቸው ሰዎች የተጠቃለለ ግምት ካሳ እንዲከፈል የተጻፉ ደብዳቤዎች እና የክፍያ መረጃ ሰነዶች በየመስተዳደሩ በተበታተነ መልኩም ቢሆን የሚገኙ መሆኑን ነገር ግን ንብረቱነቶቹንና ባለይዞታዎቹን የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች ብዙውን ጊዜ የሚገኙት የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ዘንድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

47. እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬት ላይ የሚገኙ ንብረቶች፤ የባለንብረቱ ማንነት፣ በመሬቱ ላይ የሚገኘው ንብረት ዝርዝር፣ ቤቱ የተሰራበት ቁስ (ማቴሪያል) ምንነት፣ በመሬቱ ላይ እየተመረተ የነበረው የሰብል ዓይነትና መጠን፣ በመሬቱ ላይ የነበሩ ቋሚ ተክሎች ወዘተ.. መረጃ በተሟላ ሁኔታ በከተማው ወይንም በወረዳው መስተዳደር አለመያዙ የተገመተው የካሳ ግምት ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ አዳጋች ከማድረጉም በላይ አላግባብ የካሳ ክፍያ እንዲፈፀም እና ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

መሬት ለልማት ሥራ እንዲለቀቅ ሲወሰን መሬቱ የሚለቀቅበት ጊዜ እና የካሳው ግምት ለባለይዞታው በቅድሚያ መገለጹንና መሬቱ በወቅቱ መለቀቁን በተመለከተ፣

48. መሬት ለልማት ስራ እንዲለቀቅ ሲወሰን መሬቱ የሚለቀቅበትን ጊዜና የካሳውን መጠን የሚጠቅስ የማስለቀቂያ ትእዛዝና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ለባለይዞታው በጽሁፍ እንዲደርሰው ሊደረግ ይገባል፡፡ ለባለይዞታውም የሚሰጠው የቅድመ ማስጠንቀቂያ

ጊዜንም በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 455/1997 መሰረት ክልሎች መመሪያ ማውጣት ያለባቸው ሲሆን የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ጊዜ ግን ከ90 ቀናት ማነስ የለበትም፡፡ ካሳ የተከፈለው ባለይዞታም ካሳ በተከፈለው በ90 ቀናት ውስጥ ይዞታውን ለወረዳው ወይም ለከተማው መስተዳድር ማስረከብ አለበት፡፡

49. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩት ጣና በለስ- ባህርዳር፣ ባህርዳር - ደ/ማርቆስ - አዲስ አበባ እና ወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታ ፕሮጄክቶች ቦታው ለልማት እንደሚፈለግና በአጭር ጊዜ ውስጥ ስራው የሚጀመር መሆኑ ለተነሺዎቹም ሆነ ለካሳ ገማች ኮሚቴዎች የተነገረው በድንገት መሆኑ፣ ለተነሺዎቹም በአዋጁ መሰረት ቢያንስ የ90 ቀን የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ያለመሰጠቱንና ህብረተሰቡ ስለሚሰራው ሥራ በቂ ግንዛቤ እና ተሳትፎ እንዲኖረው ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

50. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው ፕሮጀክቶች መካከል ባህርዳር - ደ/ማርቆስ - አዲስ አበባ እና ወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ለልማት አገልግሎት ተብሎ ከይዞታቸው ለተነሱና ንብረት ለተነጻባቸው ባለይዞታዎች በአዋጁ መሰረት በቅድሚያ ካሳ ሳይከፈላቸው የተነሱ መሆኑ እና በ2004 በጀት ዓመት የካሳ ክፍያ ግምት ተሰርቶላቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የካሳ ክፍያ ያልተፈጸመላቸው ባለይዞታዎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የጉራጌ ዞን ምስቃን ወረዳ (ጃሌ 1ኛ ቀበሌ)፣ የሀዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ (ታች ሀምቢቾ፣ ሰቻ ሮማ እና ከምቢቾ ጎዴ ቀበሌዎች) ባለይዞታዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡

51. ከዚህ በተጨማሪም የወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ለመዘርጋት በወሰደው የቻይና ተቋራጭ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ ውስጥ ለልማት አገልግሎት ተብለው ንብረት ለተነጻባቸው ባለይዞታዎች ክፍያ ሳይፈጸም ቤትና ሰብላቸው በዶዘር እየታረሰ እንዲነሳ የተደረገ መሆኑ፣ የተገመተው የካሳ ክፍያ ሳይከፈላቸው አንድ ዓመትና ከአንድ አመት በላይ የቆየ መሆኑን የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጉራጌ ዞን የምስቃን ወረዳና የሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ መስተዳደር ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

52. ስለሁኔታው የኮርፖሬሽኑ የ400 ኪ.ቮ ፕሮጄክት ማናጀር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኮርፖሬሽኑ ለልማት አገልግሎት በሚል ሰበብ ካሳ ሳይከፈል ከይዞታ የማፈናቀል መብትም ሆነ ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ በኮንትራክተሩና በወረዳው አስተዳደር መካከል በሚደረግ ስምምነት ለስራ ሲባል ባለይዞታውን በማግባባትና በማሳመን አልፎ አልፎ አንዳንድ ቦታዎች ከፍ ብሎ በተገለፀው ሁኔታ በወረዳው ሙሉ ኃላፊነት ተከስቶ ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ ልማቱን የሚያሰራው አካል

አስቀድሞ ቦታው በወቅቱ እንዲለቀቅለት ባለማሳወቁ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

53. በአዋጁ መሰረት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥና እና ካሳ በቅድሚያ ሳይከፈል ባለይዞታዎችን በድንገት እነርሱንም ሆነ ንብረታቸውን እንዲነሳ መደረጉ ህብረተሰቡን ለከፋ ችግር የሚዳርግ የስነልቦና ጉዳት የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ለልማት ሥራ ቦታውን የማስለቀቅ ኃላፊነት ባለባቸው የመስተዳደር አካላት ላይ ከፍተኛ የሥራ ጫና ይፈጥራል፡፡

ንብረትን የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪን የሚሸፍን ካሳ መከፈሉን በተመለከተ፣

54. ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና ሊተከልና እንደነበረ አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ንብረት ንብረቱን ለማንሳት፣ ለማጓጓዝ እና መልሶ ለመትከል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን የሚሸፍን ካሳ ሊከፈል ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ካየናቸው ፕሮጀክቶች መካከል ባህርዳር - ደ/ማርቆስ - አዲስ አበባ እና ወላይታ ሶዶ - አዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ለልማት አገልግሎት ተብለው ከይዞታቸው ለተነሱና ንብረት ለተጎዳባቸው ባለይዞታዎች በአዋጁ መሰረት የካሳ ገማች ኮሚቴው የካሳ ክፍያውን ዋጋ ሲተምን ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ንብረት፣ ንብረቱን የማንሻ፣ የማጓጓዣ እና መልሶም የመትከያ ወጪዎችንም ከዋናው የንብረት ካሳ ክፍያ ጋር በመጨመር ግምቱን በመስራት ለተነሺዎች እንዲከፈላቸው አለመደረጉ ታውቋል፡፡

56. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የካሳ ግምት ሲሰላ የማንሻ፣ የማጓጓዣና የመልሶ መትከያ ወጪ አብሮ እንዲሰላ ያልተደረገበት ምክንያት ይህ ወጪ ተጨምሮ ካሳ መሰላት እንዳለበት ግንዛቤ ስለሌላቸው መሆኑን የገማች ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ገልጸዋል፡፡

57. ለልማት አገልግሎት ከሚፈለግ መሬት ላይ ተነስቶ እንደገና ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ንብረት ያላቸው ተነሺዎች በአዋጅ የተሰጣቸው የሚነሳ ንብረትን የማንሻና የማጓጓዣ ካሳ የማግኘት መብታቸው አለመጠበቁ ተነሺዎቹ ለአላስፈላጊ ወጪ እንዲዳረጉ ከማድረጉም በላይ በልማቱ ስራ ቀና አስተሳሰብ እንዳይኖራቸውና ለልማት ተባባሪ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

ለልማት ሥራ የሚፈለገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ለአላቸው አካላት መድረሱን በተመለከተ፣

58. ኮርፖሬሽኑ ለልማት አገልግሎት የሚፈልገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ስፍራ የሚገልጽ መረጃ በማዘጋጀት ሥራው ከመጀመሩ ቢያንሰ ከአንድ አመት በፊት መሬቱን ለማስለቀቅ ሥልጣን ለአላቸው አካላት በመላክ ቦታው እንዲፈቀድ ወይም እንዲለቀቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው በአማራ ክልል የባህርዳር ከተማ፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያና የይልማና ዴንሳ ወረዳዎች የጣና- በለስ-- ባህርዳር 400 ኪሎ ቮልት እና የባህርዳር- ደብረማርቆስ 400 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክቶች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን የምስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ የወላይታ ሶዶ- አዲስ አበባ 400 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት በየትኛው መስመር እንደሚያልፍ የሚያሳይ መረጃ አስቀድሞ እንዳልደረሳቸው፣ ይልቁንም መስመሩን የሚዘረጉት ኮንትራክተሮች የሚነሳበት ቦታ ላይ ምልክት እያደረጉና ቀለም እየቀቡ የካሳ ክፍያ ግምት እንዲገመት እንደሚደርጉና ሥራቸውን ለማስጀመር በተቻለ ፍጥነት ባለይዞታዎቹን በማስነሳት ስፍራው እንዲለቀቅ ኮርፖሬሽኑ የሚያጣድፋቸው መሆኑን የየወረዳዎቹ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

60. የጣና በለስ - ባህርዳር የ400 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታ መስመሩን ለመዘርጋት ሲባል በባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ካሳ ተከፍሎ ሰዎች ከተነሱ በኋላ መስመሩ የሚያልፈው በግንቦት ሃያ (ባህርዳር) አየር ማረፊያ ክልል ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ወደ 12 የሚጠጉ ምሰሶዎች ከተተከሉ በኋላ መስመሩ በአየር ማረፊው አካባቢ ማለፍ እንደሌለበት ተቃውሞ በመቅረቡ ድጋሚ የመስመር ለውጥ ተደርጎ ሌሎች ሰዎች እንዲነሱና ሌላ ተጨማሪ መጠኑን ማወቅ ያልቻልነው የካሳ ክፍያ እንዲፈፀም የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

61. የመስመር ዝርጋታው የአዋጭነት ጥናት ሲጠና መስመሩ በአየር ማረፊው ክልል ውስጥ መሆኑና ለበረራ ችግር የሚፈጥር ወይም የማይፈጥር ለመሆኑ ከባለድርሻ አካላት ምክክር ያልተደረገበትና በጥናቱ ወቅት ይህ ከግንዛቤ ያልገባበትን ምክንያት የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው ምላሽ አልሰጡም፡፡

62. ለልማት አገልገግሎት የሚፈለገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ስፍራ የሚገልፅ መረጃ በቅድሚያ ለወረዳ/ ከተማ መስተዳደሮች እንዲደርስ አለመደረጉ፣ ከቦታው የሚነሱ የህብረተሰብ ክፍሎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ግንዛቤ

እንዲኖራቸው ካለመደረጉም በላይ መንግስትንም ሆነ ህብረተሰቡን ለአላስፈላጊ ወጪ እና የጊዜ መባከን ይዳርጋል፡፡

ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለሚለቀቅ መሬትና ንብረት የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎች ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል (በኮርፖሬሽኑ) የሚሸፈን መሆኑን በተመለከተ፡-

63. ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለሚለቀቅ መሬትና ንብረት የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች (የኮሚቴ አባላት የአበል ክፍያ እና የጽህፈት ማሳሪያ የመሳሰሉ ወጪዎች) ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል (በኮርፖሬሽኑ) ሊሸፈን ይገባል፡፡

64. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ባህርዳር- ደብረማርቆስ- አዲስ አበባ 400 ኪሎቮልት ኃይል ማስተላፊያ ፕሮጀክት እና የወላይታ ሶዶ- አዲስ አበባ 400 ኪሎቮልት የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጄክቶች የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል (ኮርፖሬሽኑ) እንዳልተሸፈኑ የገማች ኮሚቴዎቹ ገልጸዋል፡፡

65. የባህርዳር ከተማ የካሳ ገማች ኮሚቴ ሰብሳቢ የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴውን ወጪ የክልሉ መንግስት ወይም ከተማ አስተዳደር የሚሸፍን መሆኑ ሲገልጹ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀዲያ ዞን የሌሞ እና የምሰቃን ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና የገማች ኮሚቴ አባላት ክፍያ እንደዘገየ እና የማቴሪያል ድጋፍም ሳይደረግላቸው በራሳቸው የጽህፍት መሳሪያና ሌሎችንም እንዲሚሉ በማድረግ የካሳ ክፍያውን ግምት እንደሰሩ ገልጸዋል፡፡

66. ለካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች የገማች ኮሚቴ አበልን ጨምሮ ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል የፕሮጄክት ሂሳብ ሳይከፈል በገማቾቹ በራሳቸው ወይም በወረዳው/ ከተማ መስተዳደሩ ወጪው እንዲሸፈን ተደርጎ የግመታ ሥራው እንዲሰራ አለመደረጉ የኮሚቴውን የሥራ ቅልጥፍና የሚያጓትት፣ በሥራው ጥራት ላይ ችግር የሚያስከትል እና በወረዳና ከተማ መስተዳደሮች በጀት ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር ይሆናል፡፡

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

67. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የሚኖርበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው የባህር ዳር-ደብረማረቆስ-አዲስ አባባ ወላይታ ሶዶ -አዲስ አበባ 400 ኮሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክቶች የክልል መስተዳደር ጽ/ቤቶች፣ የከተማና የወረዳ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እንደዚሁም የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴዎችም ሆነ ከካሳ ከፋዮች (ኮርፖሬሽኑም) ጋር ካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ከክልሎችና ከልማት ፈጻሚ አካላት ጋር የምክክር መድረክ የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

69. ስለጉዳዩ የአማራ ክልልና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ኃላፊዎች ተጠየቀው በሰጡት መልስ ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

70. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች ካሳ ክፍያን አስመልክቶ የካሳ ክፍያ ከሚመለከታቸው የልማት ሥራ ባለቤቶችም ሆነ ከክልሎች ጋር ግንኙነት አለማድረጉ እና የምክክር መድረክ አለማዘጋጀቱ ሥራው በተቀላጠፈ መንገድ እንዳይከናወን እና በሥራ ላይ ለሚጋጥማቸው ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ እንዳይገኝ ያደርጋል፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ

71. ለልማት ሥራ ሲባል እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬት እና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እንዲሁም በንብረቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል የሚከፈል ካሳ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን የልማት ሥራ ለማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሰራር ግድፈቶችና ክፍተቶች ተገኝተዋል፡፡

72. እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬት እና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ለሚከፈል ካሳ የአከፋፈል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- ❖ አዋጅ ቁጥር 455/1997 እና እርሱን መሰረት አድርገው የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ያላወጡ ክልሎች መኖራቸው፣
- ❖ ክልሎች የካሳ አከፋፈል መመሪያ ሲያወጡ አገር አቀፉን ቀመር ተከትለው ማውጣታቸውን ለማረጋገጥ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ፣
- ❖ የካሳ ክፍያን አስመልክቶ የወጣው የካሳ አተማመን ቀመር የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በአገናዘበ መልኩ ኃላፊነት በተሰጠው አካል በየጊዜው ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑ፣

73. የካሳ ክፍያን ለማስፈጸም፣ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተልና ለመገምገም ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፣

- ❖ ለሌላ አገልግሎት ለሚለቀቅ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የካሳ ክፍያን ለመገመት የወረዳው ወይንም የከተማው አስተዳደሮች ለሚሰይሟቸው የካሳ ገማች ኮሚቴ አባላት የካሳ አከፋፈልን በተመለከተ የወጡ አዋጅ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ በቂ ገለጻ ወይም ስልጠና እንዲያገኙ አለመደረጉ፣
- ❖ እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኙና ካሳ የተከፈለባቸው ንብረቶችን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ በሚመለከት በወረዳው ወይም በከተማው መስተዳደሮች በኩል ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ፣
- ❖ መሬት ለልማት ሥራ እንዲለቀቅ ሲወሰን መሬቱ የሚለቀቅበትን ጊዜ በመጥቀስ ቢያንስ የ90 ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በጽሁፍ ለባለይዞታዎች የማይሰጥ መሆኑ፣
- ❖ ለካሳ ክፍያ ግምት በኮርፖሬሽኑ የአዋጭነት ጥናት ላይ የተመለከተው እና የካሳ ገማች ኮሚቴ የሚጠቀሙት መረጃ የተለያየና የማይናበብ መሆኑ፣

- ለልማት ሥራ ሲባል ከሚገኙበት መሬት ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ለሚደረጉ ተነሺዎች የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪን የሚሸፍን ካሳ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ መሆኑ፣
- ለሥራ የሚፈለገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ ቦታውን ለልማት በሚፈልገው አካል (በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን) ተዘጋጅቶ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ለአላቸው አካላት ያልደረሰ መሆኑ፣
- ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለሚለቀቅ መሬትና ንብረት የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎች በአስፈጻሚው መ/ቤት (በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን) አለመሸፈኑ፣
- የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልባቸው ህጎችና ደንቦች በሁሉም ክልሎች ወጥ በሆነ ሁኔታ ስለመከበራቸው በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ

ታውቋል፡፡

74. ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

75. እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬት እና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ለሚከፈል ካሳ የአከፋፈል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

   - የፌዴራል ጉዳይ ሚኒስቴር የአዋጅ ቁጥር 455/1997 ድንጋጌዎች በሁሉም ክልሎች መከበራቸውን ሊከታተልና ለልማት ሥራ ለሚፈለግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል የካሳ ግምት በተመለከተ ክልሎች አገር አቀፍ ቀመርን መሰረት ያደረገና የተጣጣመ የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጡ ይገባል፡፡ ለክልሎች አዋጁን ለማስፈፀም እንዲችሉ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድግፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
   - የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ እያገናዘበ በየጊዜው ወቅታዊ መደረጉና በክልሎችም የወጡ መመሪያዎች በዛው መሰረት ወቅታዊ መሆናቸውን በማረጋገጥ የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልባቸው ድንጋጌዎች በሁሉም ክልሎች በተጣጣመ መልኩ ለመከበራቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

76. የካሳ ክፍያን ለማስፈጸም፣ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተልና ለመገምገም ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ ፣

   - ለልማት ስራ የሚፈለገው መሬት የሚገኝበት የወረዳው ወይንም የከተማው አስተዳደር ለልማት ሥራ ሲባል የሚለቀቅ መሬትና በላዩ ላይ ያለ ንብረትን እንዲገምቱ የሚቋቋሙት የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ አባላት አዋጅ ቁጥር 455/97፣ ደንብ ቁጥር135/99 እና ሌሎች የካሳ ክፍያ የአፈፃፀም መመሪያዎችና አሰራሮችን በተመለከተ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት አስፈላጊው ገለጻ እና ሥልጠና እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡
   - የካሳ ክፍያ ተከፍሎ ለልማት አገልግሎት እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬትና በመሬቱ ላይ ስለሚገኙት ንብረቶች፣ ለካሳ ክፍያ ተመን መነሻ የሆኑ ሰነዶችና የተከፈለው የካሳ ክፍያ መጠንን የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች መሬቱንና ንብረቱን ባስለቀቀው የከተማው ወይንም የወረዳው አስተዳደር ሊያዝ ይገባል፡፡
   - ለልማት ስራ የሚፈለግ መሬት እንዲለቀቅ ሲወሰን የሚለቀቅበት ጊዜና የካሳው ግምት በአዋጅ ቁጥር 455/1997 መሰረት ቢያንስ የዘጠና (90) ቀናት

የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለባለይዞታው በጽሁፍ ሊደርሰው ይገባል፡፡ ካሳ የተከፈለው ባለይዞታም ካሳ በተከፈለው በ90 ቀናት ውስጥ መሬቱን ለሚመለከተው የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር እንዲያስረክብ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ❖ ለካሳ ግምት የአዋጭነት ጥናት እና የገማች ኮሚቴዎች የሚጠቀሙባቸው መረጃዎች እርስ በእርስ የሚናበቡና ይፋዊ ከሆኑ አገር አቀፍ ስታትስቲካዊ መረጃዎች ጋራ መጣጣማቸው እየተረጋገጠ ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡
- ❖ ለልማት ሥራ የሚነሳ ንብረት ካሳ ግምት ሲሰራ ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና ሊተከልና እንደነበረ አገልግሎት ለመስጠት የሚችል ንብረትን ለማንሳት፣ ለመጓጓዝ እና መልሶ ለመትከል የሚያስፈልጉ ወጭዎች አብረው ተካተው የሚሰራበትና የሚከፈልበት አሰራር በአዋጁ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ መሬትና ንብረትን ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ የኮሚቴ አባላት የአበል ክፍያ እና የተለያዩ ወጪዎች ቦታው ለልማት ሥራ እንዲለቀቅለት በሚጠይቀው አካል (በኮርፖሬሽኑ) በአዋጁ መሰረት ሊሸፈን ይገባል፡፡
- ❖ ኮርፖሬሽኑ ለልማት አገልግሎት የሚፈልገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ መሬቱን ለማስለቀቅ ሥልጣን ለአላቸው የከተማ ወይንም የወረዳ አስተዳደር አካላት በአዋጁ መሰረት ከአንድ አመት በፊት ሊሰጣቸውና አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲደርጉ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የሚኖርበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

77. በአጠቃላይ ለልማት ስራ እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኙ ንብረቶች የሚከፈል የካሳ ክፍያን አስመልክቶ ትክክለኛ መረጃ መያዙ እና መረጃው ለሚመለከተው አካል መድረሱ፣ እንደዚሁም የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ ሊሰራበት የሚችል የአተማመን ቀመርና የአፈፃፀም መመሪያ መውጣቱና ወቅታዊ መደረጉን፣ የካሳ ክፍያ ድንጋጌዎች በትክክል ተግባራዊ መሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉ እና የቴክኒክና የአቅም ግንባታና ድጋፍ መደረጉ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሆነ ሌላ ለልማት ሥራ ቦታ እንዲለቀቅለት የሚጠይቅ የመንግስት አካልም ሆነ የግል ባለሀብቶች በተቀላጠፈና ፍትሀዊ በሆነ ሁኔታ የልማት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ያግዛቸዋል፡፡

ይህም ስራ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴርንም ሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከካሳ ክፍያ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላትን የማስተባበርና ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

78. በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ ኮርፖሬሽኑን በቀጥታ የማይመለከቱ ቢኖሩም ኮርፖሬሽኑ በዋነኛነት የተቋቋመበትን ዓላማና ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴርም በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት ከክልሎች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ለሚመለከታቸው አካላት ጉዳዩን በማሳወቅ፣ በመከታተልና በመቆጣጠር ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

79. በመጨረሻም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን፣ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እና የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ አባላት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1፡- የኦዲት መገምገሚያ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
1. እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬት ና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ለሚከፈል ካሳ የአከፋፈል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ	1. እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬት እና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል የካሳ ግምት የሚወጣውን አገር አቀፍ ቀመር መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 4 ተ.ቁ.1
	2. አገር አቀፍ ተመኑን መሰረት በማድረግ ክልሎች ለአፈጻጸሙ መመሪያ ሊያወጡ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ
	3. ለልማት አገልግሎት በሚለቀቅ የመሬት ይዞታ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል ካሳ ንብረቱን ባለበት ሁኔታ ለመተካት የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 7 ተ.ቁ.2
	4. በመሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ መሻሻል የሚከፈል ካሳ በመሬቱ ላይ የዋለውን ገንዘብና የጉልበት ዋጋ የሚተካ ሊሆን ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 7 ተ.ቁ.4
	5. ለልማት ሥራ ሲባል ከሚገኝበት መሬት ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና ሊተከልና እንደነበረ አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ንብረት ንብረቱን የማንሻ፣የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪ የሚሸፍን ካሳ ሊከፈል ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 7 ተ.ቁ.5
2. የካሳ ክፍያን ለማስፈጸም፣ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተልና ለመገምገም ኃላፊነት የተሠጣቸው አከላት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የሆነ መሆኑን መገምገም፣ 2.1. የንብረት ግማች ኮሚቴ ሥራውን የሚያከናውንበት የአሰራር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ	6.ለካሳ ክፍያ ንብረት ለመገመት የወረዳው ወይንም የከተማው አስተዳደር ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት የሚገኙበት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 10 ተ.ቁ.1
	7.ለልማት ሥራ ሲባል ከሚለቀቀው መሬት የሚነሳው ንብረት የተለየ እውቀትና ልምድ የሚጠይቅ ሲሆን የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር የተለየ ሙያ ያላቸውን አበላት ሊሰይም ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 7 ተ.ቁ.3
	8.ንብረት ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች አግባብ ካላቸው የፌዴራል፣የክልል ወይም ሌሎች አከላት ሊጠየቅ/ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ ደንብ ቁጥር 135/99 አንቀጽ 20 ተ.ቁ 1
	9.የተሰበሰቡት መረጃዎችም በአግባቡ ሊያዙና ሊደራጁ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ
	10.የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኙትን ንብረቶች በሚመለከት መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ ደንብ ቁ.135/99 አንቀጽ 21
	11.በወረዳው ወይም በከተማው አስተዳደር የሚሰበሰበው(የሚያዘው) መረጃ ለካሳ ክፍያ ግምት መነሻ ደጋፊ የነበሩትን በሙሉ የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባል፡፡
	12.ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም አካል የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታና ካሳ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ ደንብ ቁ.135/99 አንቀጽ 22
	13. መሬት የማስለቀቂያ ትእዛዝን ለማሳወቅ የሚሰጠው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጊዜ መመሪያ ሊወጣ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ 455/97 አንቀጽ 4 ተ.ቁ.2
2.2.የወረዳና የከተማ አስተዳደሮች የካሳ ክፍያን በማስፈጸም ረገድ	14.መሬት ለልማት ሥራ እንዲለቀቅ ሲወሰን መሬቱ የሚለቀቅበትን ጊዜ በመጥቀስ እና የካሳውን ግምት በመግለጽ የማስለቀቂያ ትእዛዝ ለባላይዞታው በጽሁፍ እንዲሰጠው ሊደረግ ይገባል፡፡ምንጭ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀ4 ተራ ቁ 1

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
ኃላፊነታቸውን ቀልጣፋና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ማረጋገጥ	15.ማስጠንቀቂያ የደረሰው ባለይዞታ ካሳ ከተከፈለው ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ መሬቱን ለወረዳው ወይም ለከተማው አስተዳደር ሊያስረክብ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ 455/97 አንቀጽ 4 ተ.ቁ.3
	18 16.የሚለቀቅ ስለመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ ለባለይዞታው ከደረሰ በኋላ ለተሰራ ወይም ለተሻሻለ ቤት፣ለተዘራ ሰብል፣ ለተተከለ ቋሚ ተክል ወይም በመሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ ካሳ እንዳይከፈል ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ ደንብ ቁጥር 135/99 ክፍል 4 ተ.ቁ 1
2.3.ካሳ ከፋዩ መ/ቤት የተሰጡትን ኃላፊነቶች ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ማከናወኑን ማረጋገጥ	17.ለሥራ የሚፈለገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ ቦታውን ለልማት በሚፈልገው የኢ.ኤ.ኃ.ኮ. ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ 455/97 አንቀጽ 5 ተ.ቁ.1
	2 18. የኢ.ኤ.ኃ.ኮ. የተዘጋጀውን መረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ላላቸው አካላት በመላክ ቦታው እንዲፈቀድ/ እንዲለቀቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ 455/97 አንቀጽ 5 ተ.ቁ.1
	19.ንብረት ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎች በአስፈጻሚ መ/ቤት (በኢ.ኤ.ኃ.ኮ.) ሊሸፈን ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ ደንብ ቁ.135/99 አንቀጽ 23 ተ.ቁ. 2
	20. በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል በመቅረብ ሊጸድቅ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 12 ተ.ቁ.3
2.4.የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሥራውን ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ማከናወኑን ማረጋገጥ	21. የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልባቸው ድንጋጌዎች በሁሉም ክልሎች ለመከበራቸው በፌዴራል ሚ/ር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 12 ተ.ቁ.1
	22. በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር ለክልሎች የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ-፤ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀጽ 12 ተ.ቁ.2
	23.የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የሚኖርበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

አባሪ 2፡የኮርፖሬሽኑ፣ የከተማ፣ የወረዳ እና የገማች ኮሚቴ የካሳ ክፍያ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (process description)

- በኮርፖሬሽኑ የአዋጭነት ጥናት፣የአካባቢና የማህበራዊ ሁኔታ ግምገማ ጥናት፣ለመልሶ ማቋቋሚያ መርሀ ግብር ጥናትይዘጋጃል
- ለሚሰራው ፕሮጀክት አንድ የሥራ አስፈጻሚ በቦታው እንዲመደብ ይደረጋል፡፡
- በተመደበው ሥራ አስፈጻሚ ሥራውን ለመጀመር የሥራውንአካባቢና መጠኑንም የሚያሳዩ ባለሙያዎች ይመደባሉ፡፡
- ስለሚነሱ ቤቶች ፣ሰብሎች እና ሌሎቸ ንብረቶች ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚገልጽ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የክልል፣የከተማና የወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤቶች ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡
- ከተነሺው ማህበረሰብ ጋር በቅድሚያ የግንዛቤ ማስጫበጫ ውይይት ይደረጋል፡፡
- በሚመለከተው የወረዳ ወይንም የከተማ መስተዳድር የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡
- የተቋቋመው ኮሚቴ የካሳ ክፍያ ግምት በማውጣት ለኮርፖሬሽኑ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡
- ባለንብረቱ የሚነሳበትን ጊዜ የተተመነውን የካሳ ክፍያ መጠን የሚገልጽ እና በዚህ መሰረትም የወረዳው፣የከተማ መስተዳድሩ ትብብር እንደሚያደርጉ የሚገልጽ መተማማኛ ተዘጋጅቶ ባንብረቱ እንዲፈርም ይደረጋል፡፡
- የተፈረመው ማስረጃም በሚመለከተው የከተማ ወይንም የወረዳ አስተዳደር ማህተም እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡
- በመጨረሻም ባለመብቱ አስፋለጊውን ማስረጃ በሚሟላት በካሳ ገማች ኮሚቴ የተተመነለትን ገንዘብ በኮሚቴው ፊት በመቅረብ ከኮርፖሬሽኑ ፈርሞ እንዲወስድ ይደረጋል፡፡

አባሪ 3፡ በሄክታር የሚመረቱ ምርቶች ልዩነት የሚያሳዩ ሰንጠረዦች

1. የኮሚቴውን እና የስታትስቲክስ ጽ/ቤት በሄክታር የሚመረቱ ምርቶች ልዩነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የሰብሉ ዓይነት	የፕሮጀክቱ ስም	የኮሚቴው ግምት በሄክታር	የስታትስቲክስ ጽ/ቤት ግምት	ልዩነት የኮሚቴው ግምት	
					በመብለጥ	በማነስ
1	ጤፍ	አሉቶ ላንጋኖ	8.6	12.4		3.9
	በቆሎ	አሉቶ ላንጋኖ	14.3	26.2		11.9
	ገብስ	አሉቶ ላንጋኖ	13.2	17.4		4.2
	ስንዴ	አሉቶ ላንጋኖ	23.2	15.6	7.6	
2	ጤፍ	አላማጣ-መሆኒ-መቀለ	19	12	7	
	በቆሎ	አላማጣ-መሆኒ-መቀለ	36	19	17	
	ገብስ	አላማጣ-መሆኒ-መቀለ	-	16.2		
	ስንዴ	አላማጣ-መሆኒ-መቀለ	-	16.4		
	ማሽላ	አላማጣ-መሆኒ-መቀለ	49	21	28	
3	ጤፍ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ		-		
	በቆሎ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ		-		
	ገብስ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ		-		
	ስንዴ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ		-		
	ማሽላ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ		16		

2. የኮርፖሬሽኑን እና የኮሚቴውን በሄክታር የሚመረቱ ምርቶች ልዩነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የሰብሉ ዓይነት	የፕሮጀክቱ ስም	የኮርፖሬሽኑ የጥናት ግምት በሄክታር	ኮሚቴው ግምት	ልዩነት የኮሚቴው ግምት	
					በመብለጥ	በማነስ
	ጤፍ	አሉቶ ላንጋኖ	10	8.6		1.4
	በቆሎ	አሉቶ ላንጋኖ	52.5	14.3		38.2
	ገብስ	አሉቶ ላንጋኖ	25	13.2		11.8
	ስንዴ	አሉቶ ላንጋኖ	30	23.2		6.8
	ጤፍ	አላማጣ-መሆኒ-መቀሌ	15	19	4	
	በቆሎ	አላማጣ-መሆኒ-መቀሌ	30	36	6	
	ገብስ	አላማጣ-መሆኒ-መቀሌ	15	-		
	ስንዴ	አላማጣ-መሆኒ-መቀሌ	22	-		
	ማሽላ	አላማጣ-መሆኒ-መቀሌ	25	49	24	
	ጤፍ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ	20	-		
	በቆሎ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ	28	-		
	ገብስ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ	24	-		
	ስንዴ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ	28	-		
	ማሽላ	ቆቃ ሁርሶ ድሬዳዋ	25	18		7

3. የኮርፖሬሽኑ ጥናት እና የኮሚቴው የካሳ ክፍያ ግምት የዋጋ ልዩነት

የፕሮጀክቱ ስም	በኮርፖሬሽኑ ጥናት ላይ ለካሳ ክፍያ የተመደበ (Estimation Cost)	*በኮሚቴው ግምት መሰረት የተከፈለ*	**ልዩነት በኮሚቴው ግምት መሰረት የተከፈለው**	
			በመብለጥ	በማነስ
አሉቶ-ላንጋ ጅኦተርማል	106,065.32	691737.28	585671.96	
አላማጣ- መሆኒ- መቀሌ ኃይል ማስተላለፍ ፕሮጀክት 230 kv	6,015,591.86	8,646,211.69	2,630,619.83	
ቆቃ-ሁርሶ- ድሬዳዋ ፕሮጀክት 230 kv	9932388.40	8,509,371.84		1423016.56